# አዳም ውስጥ ያሉ ገፀ-ባህርያት

Ben Ephrem

አዳም ውስጥ ያሉ ገፀ-ባህርያት ሞራል ፓሊስ አይደሉም፤ ግንኙነቶች መልካም ይሁኑ ምናምን ብለው ሊሰብኩ አይሞክሩም (ጆርጅ ኢሌታዊ-- ዲክተም የላቸውም)

ንጥር ዱርዬዎች (ንጥር ቅቤ እንደሚባለው- በቁዋንቁዋ ቅመም የተነጠሩ) በዕውን አለም ግዘፈ-ስጋ ቢነሱ ሊደብሩኝ የሚችሉ ገፀ-ባህርያትም አሉበት፡፡

ለኔ ግን፣ ከትውልዴ፣ ‹‹ያ-ትውልድ›› አስቀረሁለት ብሎ ከሚፎክረው በኩራት ከተሞላ የቀውስ ወለላ፣ ከሉላዊነት ነቀርሳ የሚፈውሰኝ ምልክት (Sign) ስላገኘሁበት! --- ሰውነት (body) የሚል ምልክት!
ያ-ትውልድ ስል፡- አብዮት የቀመረበት (''ይሄ ትውልድ ቂልና የማያነብ ነው'' እያለ አሁንም የሚቆምርብኝ)---- አዳም እንዲህ የገለፃቸው…

‹‹ያላቸውን ደካማ ዕውቀት ሰብስበው ጠማማ ፍቅርና ጥላቻ በመፈልሰፍ ላይ እንደሆኑ መገመት አልከበደኝም፡፡ በትግል ምናምን አዋከበው መድረክ ላይ ያወጧት ግብዣ ሲያደርጉዋት ነው፤ (ያላያችሁዋት ካላያችሁ ይህቺትና ተባረኪ አሌክስን ኑና ፈንግሉ)… የሚሉዋት)››

አዳም የሚነግረኝ (እኔም ለልቤ የማስረዳው) ሴቲቷን (መዋቅሩዋን) ከአንድ ሰው ዕቅፍ አውጥቶ ለብዙሃኑ ጥቅም ማዋልን ነው፡፡ እንደ ኮሚዩኒስቶቹ አባባል ''The Joy of collective love''

የሴት ገላ የሁሉም ሲሆን ቅናት ይቀራል-- ከዚያ ቀናዒ የምትሆነው ለአብዮቱ ብቻ ነው! የምስራቅ ጀርመንን ኮሚዩን 1ን ታሪክ እንዳለ መገልበጣቸው ይሆናል ያኔ --- ፍሪ ላቭ የሚሉት አይነት፤
''We abandon jealousy and individualism to reach the joy of collective love---'' እንደማለት -
ባዮ-ፓለቲክሱ (ኮሚኒየስቶቹ የሚቆምሩበት የሰውነት ፓለቲካ) ተባረኪን ሌላ ሴት (Autre body) አድርጓታል፡፡ እነ ማርክስ ብለውት እንደነበረው:

The body had been disorganized by capitalism (of bourgeois sexual morality)፡፡
እሱም (ኮሚዩኒዝም) በተራው እድሉን ሲያገኝ ደግሞ ሰውነትን (body) ወደ ቀለጠ መሳሪያነት ለወጠው (The body was transformed into a site of resistance)

ይሄ ይሄ ትርጉም የተዛነፈበት አል-ኣዛር መጨረሻ ላይ አውሬ ይሆንና ከመውደድ በላይ/የሚያመልካትን ሴት ይደፍራታል

(እንደ-ፍቅረኛ ሳይሆን እንደጠላት ነው በመድፈር የተሰናበተኝ ትላለች ተባራኪ ራሷ! ህ!)

እኔ ዘመን ላይ የደረሰው የፍቅር ዝግመተ-ለውጥ ይሄ የዚያ ትውልድ ረጅም-ዕጅ እንዳለበት አዳም በረቂቅ ነግሮኛል--- (Unlike Hiwot's Tower in The Sky)

ከትውልዴ ስል፡- (ሮላንድ ባርዝስ Fragments of A Lover's Discourse ላይ እያንዳንዱዋ የፍቅረኞች እንቅስቃሴን ሴሚየቲክስያዊ ሲያደርገው

(One of the most important characteristics of falling in love is the existence of signs…. the lover is a natural semiotician, he sees signs everywhere and in everything."

እኔ ግን ምልክቶች አይታዩኝም-- ገላ ብቻ ይታየኛል፤ መታጠፍ የሌለበት የአፍቃሪ-ተፈቃሪ ድራማ ምልክቴን በቀሙብኝ ቅድም በጠቀስኳቸውና ሌሎች አደባባይ በማላወጣቸው ነገሮች ሁላ ታጥፎብኛል፤ ለዚያ ነው በፍቅር መውደቅ ያቃተኝ፤

ያ የሃገሬ ሴት ፊት ላይ አየው የነበረው ደብተራዊ ሃረግ (ወይ Cabalistic Phrase በሉት ከፈለጋችሁ)፣ የሚያደናግረኝ፣ የሚያደናግጠኝ፣ የሚያፈላስፈኝ (አሁን የዘፈን ገጣሚዎቻችን ሳይቀር የጠፋባቸው--ሲያስቅ!) በስንት ሰዓታት የስልክ ንግግር ወይ በፌስ ቡክ፣ ቫይበር፣ ኢሞ፣ ዋትሳፐ ተነርቶ የጠፋው… የመጀመሪያው ቀን ሳገኛት የሚገለፅልኝ ጭልታ ቢኖር ‹‹የቀረን አንሶላ መጋፈፍ ብቻ እኮ ነው›› የሚል ሃረግ ነው
እና አንሶላውን ብቻ ሳይሆን እንደ አውሬ አልጋ ላይ ቆዳችንን እንጋፈፋለን (የኔ ታሪክ Accumulation of F?#%C Bodies! መሆኑ ነው - የሆቫርትን ሃረግ ልጠቀምና)

(ከብዙ ሴቶች ጋር ነኝ፤ ካንዱዋም ጋር ግን አይደለሁም) እና ድብን ያለ ድብርት ውስጥ እገባለሁ፣ መገንጠል፣ ---፤ ተምኔታዊ የሚመስለው፣ ቂላቂል የሚመስለው ምልክታዊነት ‹‹ሁዋላ-ቀርነት›› ምናምን አልነበረም ለካ! (መፋዘዙ፣ መደነባበሩ፣ መግደርደሩ፣ ይሉኝታው ምናምኑ..) … እሱ እሱ ምልክት አዳም እንዳይጠፋ ለፍቷል፡፡

አዳም በድብርት የተበላውን የስጋዬን ክፍል እንደ ቀልድ በረሳሁት ምልክታዊ አለም ሊሞላ ላቡን ጠብ ማድረጉ!-- አነበዋለሁ ለዚያ ለዚያ-- ለሱ በትክክልም A Lover is a natural semiotician!

(ለምሳሌ በትንሹ፡- ጅማወርቅ (የስንብት ቀለማት) የምልክቶች ደብተራ አይደለችምን-----‹‹እንዳንዳንድ ሴቶች በመረጃቸው እንደሚሸረሙጡ ከማንም መረጃ ለቃቅሜ መጥቼ ተክዬን አልመዘንኩትም…›› )

ሉላዊነት ስል፡- Ne pas cede sur son desir /በፍፁም ፍላጎትህን አትገድበው/ የሚል (ጃክ ላኮያዊ ድህረ-ዘመናዊነት (አይ-ዘመናይ እቴ)--- በነዚያም በነዚህም ተዘናግቼ ሳለ እንደ ገደል ናዳ የሚወርድብኝን አሜሪካ ለኔ ያስቀመጠችልኝን ህልም (American Dream) ከፓርኖግራፊ፣ በርገርና ኮካ ኮላ ጋር ሳጣጥመው--- ሰውነት (body) የሚለው ፅንሰ-ሃሳባቸው ሃሳቤ ነው

Obsessed with physiological material efficiency (machination--- )--

የገዛ ራሳቸው ሊቀ-ምሁራን ላርኮ ተስፋ በቆረጠ ቅላፄ እንዳለው - Sex as essentially a body function (ህም..)--- ይሄው እዚሁ ሃገሬ የገዛ ዘመኔ ውስጥ ስነ-ፅሁፉ፣ ሲኒማው ዘፈኑ ውስጥ መባያ አድርገውት (የት ሄጄ ልፈንዳ?! አለች)

አዳምስ?

"ወሲብን እፅፋለሁ ግን ማወቅን ያላስቀደመ ነገር አልፅፍም" ይላል!---

(ታላቁን ስብሃት በቀይ-ሌሊት ሲገስፀው--- ከፐርፎርማንስ እውቀት ይቅደም ይለዋል-- (እቴሜቴ የሎሚ ሽታ)--- ይሄ ደግሞ እስከ ስንብቱ ቀለማት ይዘልቃል----

እነዚህ ምልክቶች--- ወደ ቀደመው ድንበሬ ከሚመልሱኝ ከጠፉብኝ ምልክቶች መሃል ጥቂቶቹ (ጥቂቶቹ) ናቸው-- ይሄ ይሄ ደግሞ (ከመ ፋጻ ቀጢን ወከመ መሰንቆ-ሃዋዝ ያስተፌሥሃኒ--- )

እንደ ረቂቅ ፉጨት፣ እንደ አማረ መሰንቆ ልቡናዬን ደስ ያሰኘኛል፤ አለቀ!

ስለዚህ እንዲህ እልሃለሁ----

ወይጠልል በቅብዕ ሲበትከ!
"ሽበትህ በቅባት ይለምልም!!"